የኢፌዴሪ የመድኃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ
FDRE PHARMACEUTICALS FUND AND SUPPLY AGENCY
የሥራ አመራር ቦርድ ጽ/ቤት
OFFICE OF BOARD OF DIRECTORS

ቁጥር ስአር/መፈአኤ/004/2009 ቀን 03/11/2009
Ref.No. Date

ለመድኃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ

<u>አዲስ አበባ</u>

የመድኃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ የስራ አመራር ቦርድ ያፀደቀውን የደንብ ልብስ፣ የአደጋ መከላከያ መሣሪያዎችና ቁሳቁሶች አፈፃፀም መመሪያ 20 ገፅ ከዚህ ሸኚ ደብዳቤ ጋር አያይዘን እየላክን መመሪያው ተፈፃሚ እንዲሆን እናስታውቃለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ቦጋለ ፈለቀ
የሥራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢ

አባሪ ፡- <u>ከላይ እንደተገለፀው</u>

<u>ግልባጭ</u>

- ✓ ለሥራ አመራር ቦርድ ጽ/ቤት
  <u>መ.ፈ.አ.ኤ</u>

ስልክ Tel. 011- 276 32 65 - ዋና ዳይሬክተር
011- 276 32 80 - የሥራ አመራር ቦርድ ጽ/ቤት
E-mail-pfsa@ethionet.et
ፋክስ (Fax) 0112 75 25 55
ፖ.ሣ.ቁ P.O.Box 21904

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
የመድኃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ
PHARMACEUTICALS FUND AND SUPPLY AGENCY (PFSA)

☎ 011-275 17 70, 011-276 06 76, 011-75 06 74   011-155 32 77, 011 275 25 55   ✉ 21904   E-mail: pfsa@ethionet.et

# የመድኃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ

# የደንብ ልብስናየአደጋ መሣሪያዎችና ቁሳቁሶች መመሪያ

## 383/2013

ሰኔ 2009 ዓ.ም.

# 1. መግቢያ

ኤጀንሲው የሰራተኞቹን ደህንነት ለመጠበቅና ሊደርሱባቸው ከሚችሉ አደጋዎች የቅድመ ጥንቃቄ እርምጃዎችን በመውሰድ ሰራተኞቹን በተሰማሩበት የስራ መስክ ስራቸውን በአግባቡ መወጣት እንዲችሉና የተሻለ ውጤት እንዲያስመዘግቡ ኤጀንሲው የደንብ ልብስና የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎችና ቁሳቁሶች አፈጻጸም መመሪያ ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኗል፡፡

በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ነሐሴ 2000 ዓ.ም በተላለፈው የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎችና ቁሳቁሶች ጥናት፣ አፈቃቀድና አፈጻጸም መመሪያ በግልጽ በተቀመጠው መሠረት መስሪያ ቤቶች ካላቸው የስራ ፀባይ አንጻር የራሳቸው የሆነ የሙያ ጤንነትና ደህንነት አጠባበቅ፣ የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎችና ቁሳቁሶች አፈቃቀድና አፈጻጸም መመሪያ ማውጣት እንደሚችሉ ይደነግጋል፡፡ በዚህም መሰረት ኤጀንሲው የደንብ ልብስና የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎችና ቁሳቁሶች አፈጻጸም መመሪያ አዘጋጅቷል፡፡

# 2. ዓላማ

የኤጀንሲውን ሠራተኞች የስራ ደንብ ልብስና የአደጋ ጊዜ መሳሪያዎች እንዲሁም ቁሳቁሶች ላይ ወጥና ግልጽነት ያለው የአሰራር ስርአት እንዲይዝ ለማድረግ ፣

# ክፍል አንድ

## አጠቃላይ

### 3.አጭር ርዕስ፡-

ይህ መመሪያ የኢ.ፌዴሪ የመድኃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ የደንብ ልብስ፣ የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎችና ቁሳቁሶች አፈጻጸም መመሪያ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

383/2013

### 1. ትርጉም፡-

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፣

1. "ኤጀንሲ" ማለት የመድኃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ ማለት ነው፣
2. "ሠራተኛ" ማለት በመድኃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ ውስጥ በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነትና በኮንትራት ተቀጥሮ የሚሰራ ማንኛውም ሰው ማለት ነው፡፡
3. "የቅርንጫፍ መ/ቤት" ማለት በኤጀንሲው ስር የተቋቋመ ቅርንጫፍ መ/ቤት ማለት ነው፡፡
4. "የደንብ ልብስ" ማለት ለሠራተኞች በስራ ላይ እያሉ ደህንነታቸውንና ንፅህናቸውን ለመጠበቅና_ለመለያነት እንዲያገለግላቸው የሚሠጥ ልብስ ነው፡፡
5. "የአደጋ መከላከያ መሣሪያዎችና ቁሳቁሶች" ሠራተኛው ከጤና ጠንቆችና አደጋዎች እራሱን ለመከላከል የሚለበሱ፣የሚደረጉ፣የሚታሠሩ፣የሚጠለቁ ወይም በጆሮ ውስጥ የሚሸጎጡ /የሚወተፉ/ መሣሪያዎች ናቸው፡፡
6. "የስራ መሳሪያ" ማለት ሰራተኛው ስራውን በጋራ ወይም በግል ለማከናወን እንዲጠቀምበት የሚሰጥና ስራውን ሲጨርስ በስራ ቦታው የሚቀመጥ ልዩ ልዩ የስራ መሳሪያ ወይም እቃ ማለት ነው፡፡
7. "ካኪ" ማለትቀለሙ እንደተፈለገ ሆኖ መቶ በመቶ ከጥጥ የተሰራ ካኪ ትዊል ነው፡፡
8. "ፖሊስተር ካኪ" ማለት ቀለሙ እንደተፈለገ ሆኖ ከጥጥ እና ጨርቁ እንዳይጨማደድ ከሚረዳ ሴንቴቲክ ጥሬ ዕቃ የተሰራ ጨርቅ ነው፡፡
9. "ቲትረን 6000" ማለት ከፖሊስተር የተሻለ ሆኖ የቀለሙ ልዩነት ሳይወሰን ከጥጥ ወይም ተመሳሳይ ከሆነ ጥሬ እቃ የተሰራ ጨርቅ ነው፡፡

10. “አንድ ወጥ ሸሚዝና ሱሪ” ማለት ከአንድ ዓይነት ጨርቅ የተሰፉ ሆኖ ያለ ኮት ሊለበስ የሚችል ሸሚዝና ሱሪ ነው፡፡

11. “ሸሚዝ” ማለት ቀለሙ እንደተፈለገ ሆኖ የሴንቴቲኩ መጠን ዝቅ ካለና የጥጡ መጠን ከፍ ካለ ለሸሚዝ እንዲሆን ከተመረተ ጨርቅ የተሰራ ነው፡፡

12. “ቀሚስ” ማለት ቀለሙ እንደተፈለገ ሆኖ ሙሉ በሙሉ ከጥጥ ወይም የጥጥና የሴንቴቲክ ድብልቅ ከሆነ ጥሬ እቃ የተሰራ ነው፡፡

13. “የውስጥ ልብስ” ማለት ቀለሙ እንደተፈለገ ሆኖ ሙሉ በሙሉ ከጥጥ ወይም ለውስጥ ልብስ አገልግሎት እንዲሆን ከተመረተ ጨርቅ የተሰራ የውስጥ ልብስ ነው፡፡

14. “ሸርጥ” ማለት ከጥጥ ወይም ከሌላ ተስማሚ ጥሬ ዕቃ የተሰራ ሆኖ የልብስን መቆሸሽ ለመከላከል የሚለበስ ነው፡፡

15. “የሴት ጫማ” ማለት መጠኑ አጭር፣ አጭር ቡትስ ወይም ረጅም ቡትስ ሆኖ ለሴቶች የሚያገለግል ቀለል ያለ ከቆዳ የተሰራ ጫማ ነው፡፡

16. “ጋዎን ወይም ሙሉ የስራ ካፖርት” ማለት ቀለሙ እንደተፈለገው ሆኖ ከቲትረን 6000 ጨርቅ የሚሰፋ ገበር የሌለው ጋዎን ወይም ሙሉ የስራ ካፖርት ነው፡፡

17. “ካፖርት” ማለት ከሱፍ የተሰራ ወይም ሙቀት እንዲሰጥ ገበር ያለው ሆኖ ከጥጥ ወይም ከሴንቴቲክ የተሰራ የብርድ መከላከያ ልብስ ነው፡፡

18. “የዝናብ ልብስ” ማለት ከጥጥና ከሴንቴቲክ የተሰራ የዝናብ መከላከያ ልብስ ነው፡፡

19. “ቱታ” ማለት ከጥጥ ወይም ከሌላ ጥሬ ዕቃ የተሰራና ሱሪው ከጃኬት መሰል ልብስ ጋር ተያይዞ የተሰፋ ሆኖ የልብስን መቆሸሽ ለመከላከል በልብስ ላይ ተደርቦ የሚለበስ የስራ ልብስ ነው፡፡

20. “አጭር ቆዳ ጫማ” ማለት ማሰሪያ ያለው ወይም የሌለው ሆኖ ለሲቪል ስራ አገልግሎት የሚውልና ቁመቱ ከቁርጭምጭሚት የማያልፍ ከቆዳ የተሰራ ጫማ ነው፡፡

21. “የላስቲክ ቦቲ ጫማ” ማለት ከተፈጥሮ ጎማ የተሰራ ገበር ያለው ሆኖ በክረምትና ጭቃ በሚበዛበት ወቅት የሚደረግና በቀላሉ የሚጸዳ ጫማ ነው፡፡

22. “አጭር ቡትስ ጫማ” ማለት ዚፕ ወይም ማሳሪያ ያለው ወይም የሌለው ሆኖ ለሲቪል ስራ አገልግሎት የሚውልና ቁመቱ ቁርጭምጭሚትን የሚሸፍን ነገር ግን ባት አሰር ያልሆነ ከቆዳ የተሰራ ጫማ ነው፡፡

23. “ረጅም ቡትስ ጫማ” ማለት ዚፕ ወይም ማሰሪያ ያለው ወይም የሌለው ሆኖ ለሲቪል ስራ አገልግሎት የሚውልና ቁመቱ ባት ላይ የሚደርስ ከቆዳ የተሰራ ጫማ ነው፡፡

## 2.የመመሪያው ተፈፃሚነት ወሰን፡-

1.ይህ መመሪያ በዋናው መ/ቤት እና በሁሉም ቅርንጫፎች ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

# ክፍል ሁለት

## ተግባርና ኃላፊነት

## 6.የሠራተኞች ኃላፊነትና ግዴታ

1. የሠራተኞችን ደህንነትና ጤንነት ለመጠበቅ የወጡ ሕጎችንና መመሪያዎችን ማክበር፡፡
2. የራሱን ወይም የሌሎችን ደህንነትና ጤንነት ለመጠበቅ የተሰጠውን የሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት መከላከያ መሣሪያዎችና ቁሳቁሶች በአግባቡ በጥቅም ላይ ማዋል፡፡
3. የሥራ ላይ አደጋ ወይም የጤንነት ችግር ሊያደርስ ይችላል ብሎ ያመነውንና በራሱ ሊያስወግደው ያልቻለውን ማንኛውንም ሁኔታ ወይም ስጋት ለስራ ክፍሉ ኃላፊ ወይም ለስራ አካባቢ ጤንነትና ደህንነት ባለሙያ ወዲያውኑ ማሳወቅ ይገባል፡፡
4. ተሰፍቶ ወይም ተገዝቶ የተሰጠውን ልብስና ጫማ በሥራ ላይ ለብሶ መገኘት አለበት፡

# ክፍል ሶስት

## 7. የደንብ ልብስና የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎችና ቁሳቁሶች ስለሚሰጥበት ሁኔታ

1. ለየስራ መደቦች የተፈቀደው የስራ ልብስ ዓይነትና መጠን የሚሰጠው በስራ መደቡ ላይ ተመድበው በመስራት ላይ ለሚገኙ ቋሚ፣ ኮንትራትና የሙከራ ቅጥር ሰራተኞች ሆነው ወዲያውኑ የደንብ ልብስ የሚያስፈልጋቸው ነው፡፡

2. የደንብ ልብስ በተፈቀደለት ስራ መደብ ላይ የተመደበ ማንኛውም ሰራተኛ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ሊሰጥ ይገባል፡፡

3. በውክልና ወይም በያዙት የስራ መደብ ላይ በተደራቢነት እንዲሰሩ ለተመደበው ሰራተኞች ለስራ መደቡ የተፈቀደው የስራ ልብስ ይሰጣቸዋል፡፡ ሆኖም የያዙት የስራ መደብ የደንብ ልብስ ያለው ከሆነና በውክልና ደርበው እንዲሰሩ የተሰጣቸው የስራ መደብም የደንብ ልብስ ያለው ከሆነ የአንዱን የስራ መደብ ብቻ መርጠው እንዲወስዱ ይደረጋል፡፡

4. የለቀቁት ሰራተኞች የወሰዱትን የስራ ልብስ እንዲመልሱ አይጠየቁም፡፡ በለቀቁ ሰራተኞች ምትክ የሚተካ ሰራተኛ ደንብ ልብስ ይሰጠዋል፡፡

5. የደንብ ልብስና የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎችና ቁሳቁሶች በተፈቀደላቸው ስራ መደቦች በመስራት ላይ የሚገኝ ሰራተኛ በተለያዩ ምክንያቶች በተከታታይ ከ6 ወራት በላይ ከስራ ገበታው ቢለይ በስራ ላልነበረባቸው ጊዜያት የደንብ ልብስና የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎች አያገኝም፡፡

6. በሞቃታማና በውርጭ አካባቢዎች የተመደቡና የስራ ልብስና መሳሪያ የተፈቀደላቸው የስራ መደቦች በመስራት ላይ ለሚገኙ ሰራተኞች በመመሪያው ከተፈቀዱት የጨርቅና የጫማ ዓይነቶች ምትክ ለአካባቢው የአየር ፀባይ ተስማሚ የሆነ የስራ ልብስና መሳሪያ ይሠጣቸዋል

# ክፍል አራት

## 8.የደንብ ልብስና የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎችና ቁሳቁሶች ዝግጅትና አሰጣጥ

1. ኮትና ሱሪ፣ ጃኬትና ጉርድ ቀሚስ፣ አንድ ወጥ ሸሚዝና ሱሪ፣ የውስጥ ልብስና ቀሚስ ለተፈቀደላቸው ሰራተኞች ሁለቱም ጨርቅ በአካባቢው የገበያ ዋጋ ከነገበሩ ኤጀንሲው አሰፍቶ ይሰጣል፡፡
2. የማሰፊያ ዋጋ ተመን በየዓመቱ ያለው የማሰፊያ የገበያ ዋጋ አንድ የዕቃ ግዥ ሠራተኛ፣ የግዢ ባለሙያና ከተጠቃሚ ተወካይ ቢጋራ በመሆን ወይም ኮሚቴ በማቋቋም ገበያውን አጥንተው በሚያቀርቡት የውሳኔ ሃሳብ ላይ በበላይ ኃላፊ ወይም በቅርንጫፍ ኃላፊ በሚሰጥ የመጨረሻ ውሳኔ መሰረት ይፈፀማል፡፡
3. በበጀት ዓመቱ ውስጥ ያልተሰጠ የደንብ ልብስ ሳይሰጥ የቀረው በአሰራር ስህተት ከሆነ የሚመለከተው አካል ተጠያቂነት እንደተጠበቀ ሆኖ ያልተሰጠው የደንብ ልብስ አይሰጥም፡፡
4. የደንብ ልብስ በዓመት ሁለት ጊዜ እንዲያገኙ ለተፈቀደላቸው ሰራተኞች የደንብ ልብሱን በየስድስት ወሩ ወይም እንደአስፈላጊነቱ በአንድ ጊዜ ሊሰጥ ይችላል፡፡
5. ኤጀንሲው እንደየስራ ፀባዩ አስፈላጊ የሆኑ የደንብ ልብስ ወይም የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎችና ቁሳቁሶች ለሰራተኛው ያቀርባል፡፡ የስፌቱን ዓይነት ወይም ሞዴል በተጠቃሚውና በግዢ ቡድን ኮሚቴ በስምምነት ይወሰናል፤ ስፌቱም በጨረታ ሆኖ በእያንዳንዱ ሰራተኛ ልክ ይሆናል፡፡
6. ለሰራተኛው የተሰጠው የስራ ልብስ ወይም የስራ ላይ አደጋ መከላከያ መሳሪያዎችና ቁሳቁሶች በስራ ላይ ሲጠቀምበት ከስራው ጋር ግንኙነት ባለው ምክንያት ቢበላሽና ከአገልግሎት ውጭ መሆኑ ሲረጋገጥ ኤጀንሲው ይተካለታል፡፡
7. የሚሰጠው ወይም የሚሰፋው የደንብ ልብስ ጨርቅ መጠን በሚከተለው ዝርዝር መሰረት ይሆናል፡፡
    1. ለወንዶች ሁለት ሙሉ ልብስ 7.00 ሜትር ይሆናል
    2. ለሴቶች ሁለት ሙሉ ልብስ 6.00 ሜትር ይሆናል
    3. ለሴቶች የውስጥ ልብስ 4.50 ሜትር ይሆናል

# ክፍል አምስት

## 9 የሚሰጠው የጨርቅና የጫማ ዓይነት

### 9.1 ለደንብ ልብስ አገልግሎት የሚውሉ የጨርቅ ዓይነቶች

1. ለቱታ፣ ለአንድ ወጥ ሽሚዝና ሱሪ፣ ለጃኬትና ጉርድ ቀሚስ፣ ለኮትና ሱሪ፣ ለሙሉ ካፖርት፣ ለጋዋንና ለሽርጥ የሚሰጠው የጨርቅ ዓይነት በሃገር ውስጥ የተመረተ ቴትረን 6000 ወይም ተመሳሳይና ተመጣጣኝ የልብስ ጥራትና የዋጋ መጠን ያለው ጨርቅ ይሆናል፡፡
2. "ብርድ ልብስ" የጨርቅ ዓይነት ሙቀት የሚሰጥ ሲሆን አንድ የመንግስት ሰራተኛ ስራውን በሚያከናውንበት ጊዜ እንደየስራው ጠባይ ከውርጭና ከብርድ ለመከላከል የሚረዳ የስራ ልብስ ነው፡፡
3. ለካፖርት የሚሰጠው የጨርቅ ዓይነት ሙቀት የሚሰጥና ገበር ያለው ሆኖ የጥጥ ወይም የሴንቴቲክ ወይም ከጥጥና ከሴንቴቲክ ጥሬ ዕቃ የተሰራ ይሆናል፡፡ ይህ የማይገኝ ከሆነ በምትኩ ሙቀት የሚሰጥና ገበር ያለው ፊልድ ጃኬት ገዝቶ መስጠት ይቻላል፡፡
4. የሚሰጠው የዝናብ ልብስ ከጥጥና ከሴንቴቲክ የተሰራ ነው፡፡
5. ካኪ ጋውን ጨርቅ ለቱታ፣ ለሙሉ የስራ ካፖርትና ለሽርጥ፣
6. ፖሊስተር ካኪ ጨርቅ ለኮት፣ ለሱሪ፣ ለአንድ ወጥ ሽሚዝና ሱሪ፣ ለጃኬትና ጉርድ ቀሚስ፡፡
7. ሙሉ በሙሉ ከጥጥ ወይም ከጥጥና ከሴንቴቲክ ድብልቅ ከሆነ ጥሬ ዕቃ የተሰራ ጨርቅ ለሴቶች ቀሚስ፡፡
8. ሙሉ በሙሉ ከጥጥ ወይም ከሌላ ተስማሚ ጥሬ ዕቃ የተሰራ ጨርቅ ለሴቶች የውስጥ ልብስ አገልግሎት ይውላል፡፡
9. የሚሰጠው የደንብ ልብስ ከመለዮ ለባሹ ጋር ተመሳሳይ እንዳይሆን ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል፡፡

10.የሚሰጠው የደንብ ልብስ አንድ ዓይነት/ቀለሙ/ ወጥነት ያለው እንዲሆን ተደርጎ ይህም ኤጀንሲው ለማስተዋወቅ ልዩ መለያ ማድረግ፡፡

## 9.2. ለስራ አገልግሎት የሚውሉ የጫማ ዓይነቶች

በወቅቱ ያለውን የገበያ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ በጥራታቸው፣ በዋጋቸውና በደረጃቸው ተመጣጣኝ የሆኑ የአገር ውስጥ ጫማዎችን ገዝቶ መስጠት ይቻላል፡፡

| ተ.ቁ | ጫማው | የጫማው ዓይነት |
|---|---|---|
| 1. | ቁመቱ ከቁርጭምጭሚት የማያልፍ ማሰሪያ ያለው ወይም የሌለው | ከቆዳ የተሰራ አጭር ጫማ ነው፡፡ |
| 2. | ዚፕ ወይም ማሰሪያ ያለው ወይም የሌለው ቁርጭምጭሚት የሚሸፍን | ከቆዳ የተሰራ አጭር ቡትስ ጫማ ነው፡፡ |
| 3. | በክረምትና ጭቃ በሚበዛበት ወቅት የሚደረግ ከተፈጥሮ ጎማ የተሰራ ገበር ያለው ሆኖ በቀላሉ የሚፀዳ | የላስቲክ ቡትስ ጫማ አገልግሎት ይውላል፡፡ |

# ክፍል ስድስት

## 10.የተፈቀደ የደንብ ልብስ ዓይነት

በዚህ መመሪያ መሰረት የደንብ ልብስ የሚያስፈልጋቸው የስራ መደቦች ላይ ለሚሰሩ ሰራተኞች የሚሰጠው የደንብ ልብስ የዚህ መመሪያ አካል በሆነው አባሪ 1 ሠንጠረዥ የደንብ ልብስ የተወሰነላቸውን የስራ መደቦች እና የተፈቀደውን የደንብ ልብስ ዓይነትና መጠን የሚያሳይ ሰንጠረዥ በሚለው ርዕስ ስር የተዘረዘረውን ያጠቃልላል፡፡

በአባሪ 1 ሠንጠረዥ ውስጥ የተመለከቱት ደንብ ልብሶች የሚሰጡት በሰንጠረዡ ውስጥ የተዘረዘሩትን ስራ መደቦች እንዲያከናውኑ ለተመደቡ ቋሚ፣ ኮንትራት ወይም የሙከራ ቅጥር ሰራተኞች ነው፡፡

# ክፍል ሰባት

## 11. የወተት አበል

1. ለጤና ጠንቅ በሆኑ ኬሚካሎች፣ ራድዮ አክቲቪ ጨረሮች፣ ብናኝ፣ ትናኝ፣ ሽታ እንዲሁም ሌሎች ለጤና ጠንቅ ናቸው በሚባሉ የሥራ መደቦች በመደበኛ ስራ ቀናትና ከመደበኛ የስራ ቀናት ውጭ ለሚከናወኑ ስራዎች ኤጀንሲው ወተት ያቀርባል ወይም በወቅቱ የገበያ ዋጋ ይከፍላል፡፡ ሆኖም ሰራተኛው በዓመት ፈቃድ ምክንያት ከስራ ገበታው ላይ በሚለይበት ወቅት ይህንን አያገኝም፡፡
2. በአባሪ 1 ሰንጠረዥ ውስጥ የተመለከቱት የወተት አበል ወይም ወተት የሚሠጣቸው በሰንጠረዡ ውስጥ የተዘረዘሩትን ስራ መደቦች እንዲያከናውኑ ለተመደቡ ቋሚ፣ ኮንትራት ወይም የሙከራ ቅጥር ሰራተኞች ነው፡፡

## 12.መመሪያዉ የሚፀናበት ጊዜ

1. ይህ የደንብ ልብስና የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎችና ቁሳቁሶች መመሪያ በስራ አመራር ቦርድ ከጸደቀበት ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

## 13.መመሪያዉን ስለማሻሻል

1.ይህ መመሪያ አንዳስፈላጊነቱ ሊሻሻል ይችላል።

# 10.አባሪ 1

1.የደንብ ልብስና የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎችና ቁሳቁሶች የተወሰነላቸውን የስራ መደቦች እና የተፈቀደውን የደንብ ልብስ ዓይነትና መጠን የሚያሳይ ሰንጠረዥ፡፡

| ተ.ቁ | የስራ መደብ | የሚሰጠው የደንብ ልብስ | ብዛት | የሚሠጥበት ጊዜ | ማብራሪያ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የጥበቃ ሰራተኛ /ወንድ/ | ኮትና ሱሪ | 2 | በየዓመቱ | |
| | | ሸሚዝ | 2 | በየዓመቱ | |
| | | አጭር የቆዳ ጫማ /ጥንድ/ | 2 | በየዓመቱ | |
| | | የሱፍ ካፖርት | 1 | በየ3 ዓመቱ | |
| | | የዝናብ ልብስ/ገበር ያለው/ | 1 | በየ3 ዓመቱ | |
| | | ኬፕ ከጨርቅ የተሰፋ (ከሚሠጠው ደንብ ልብስ ጋር ተመሳሳይ ቀለም ያለው) | 2 | በየዓመቱ | |
| | | ባትሪ /የእጅ/ | 2 | እንዳለቀ ነገር ግን ያለቀበት ምክንያት አሳማኝ ሲሆንና ዕቃው ገቢ ሲደረግ | በጋራ ስቲም የሚጠቀሙበት |
| | | ዣንጥላ | 1 | በየ2 ዓመቱ | |
| | | ብርድ ልብስ/ለግል/ | 1 | በየ3 ዓመቱ | |
| | የጥበቃ ሰራተኛ /ወንድ/ | የልብስ ሳሙና 250 ግራም | 1 | በየወሩ | |
| | | የስፖንጅ ፍራሽ 1 ሜትር | 1 | በየ3 ዓመቱ | በጋራ ስቲም |
| | | ከረቫት(ከሚስጠቀው ደንብ ልብስ ጋር | 2 | በየዓመቱ | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ተስማሚ) | | | |
| 2 | የጥበቃ ሰራተኛ /ሴት/ | ኮትና ጉርድ ቀሚስ | 2 | በየዓመቱ | |
| | | የውስጥ ልብስ | 2 | በየዓመቱ | |
| | | የልብስ ሳሙና 250 ግራም | 1 | በየወሩ | |
| | | የዝናብ ልብስ/ኀበር ያለው/ | 1 | በየ3 ዓመቱ | |
| | | ኬፕ ከጨርቅ የተሰፋ | 2 | በየዓመቱ | |
| | | አጭር ቆዳ ጫማ | 2 | በየዓመቱ | |
| | | ሸሚዝ (የሴት) | 2 | በየዓመቱ | |
| | | ዣንጥላ | 1 | በየ2 ዓመቱ | |
| | | ከረቫት(ከሚሠጠው ደንብ ልብስ ጋር ተስማሚ) | 2 | በየዓመቱ | |
| 3 | ሾፌርና የሾፌር ረዳት | ኮትና ሱሪ | 2 | በየዓመቱ | ብርድ ልብስና ፍራሽ የሚሰጠው 35 ኩንታልና ከዚያ በላይ መጫን አቅም ላላቸው አሽከርካሪዎችና ረዳቶች ነው |
| | | ሸሚዝ | 2 | በየዓመቱ | |
| | | የልብስ ሳሙና 250 ግራም | 2 | በየወሩ | |
| | | አጭር የቆዳ ጫማ | 1 | በየዓመቱ | |
| | | አጭር ቡትስ የቆዳ ጫማ | 1 | በየዓመቱ | |
| | ሾፌርና የሾፌር ረዳት | | | | |
| | | ካኪ ቱታ | 2 | በየዓመቱ | |
| | | ብርድ ልብስ/ለግል/ | 1 | በየ3 ዓመቱ | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ፍራሽ /0.90 ሜትር/ | 1 | በየ3 ዓመቱ | |
| | | የእጅ ባትሪ ትንሿ | 1 | እንዳለቀ | |
| | | አካፋና ዶማ/ለሾፌር/ | 1 | በየ3 ዓመቱ | |
| | | የዝናብ ልብስ (ገበር ያለው) | 1 | በየ3 ዓመቱ | |
| | | ወፍራም የእጅ ጓንት /ከቆዳ የተሠራ | 2 | በየዓመቱ | |
| 4 | የተሽከርካሪ ጥገና ኦፊሰር | ቱታ | 2 | በየዓመቱ | |
| | | ካኪ ካፖርት | 1 | በየዓመቱ | |
| | | ሴፍቲ ጫማ /ጥንድ/ | 1 | በየዓመቱ | |
| | | የልብስ ሳሙና 250 ግራም | 2 | በየወሩ | |
| | | የእጅ ጓንት | 2 | በየዓመቱ | |
| 5 | ፖስተኛ /ሞተረኛ/ | ጃኬት /ቆዳ መሰል/ | 2 | በየዓመቱ | |
| | | ኮትና ሱሪ | 2 | በየዓመቱ | |
| | | ሸሚዝ | 2 | በየዓመቱ | |
| | | የልብስ ሳሙና 250 ግራም | 1 | በየወሩ | |
| | | ሴፍቲ ጫማ /ጥንድ/ | 2 | በየዓመቱ | |
| | | ረጅም ቡትስ ቆዳ ጫማ | 1 | በየዓመቱ | |
| | | የብረት ቆብ/ሄልሜት/ | 1 | እንዳለቀ | |
| | | የዝናብ ልብስ /ባለገበር/ | 1 | በየ3 ዓመቱ | |
| | | የወፍራም እጅ ጓንት /ከቆዳ የተሠራ | 2 | በየዓመቱ | |
| | | የንፋስ መነጽር | 1 | በየዓመቱ | |

FDRE Pharmaceuticals Fund And Supply Agency Office of Board of Directors

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 6 | አትክልተኛ /ወንድ/ሴት | ኮትና ሱሪ | 2 | በየዓመቱ | |
| | | ኮትና ቀሚስ/ለሴት/ | 2 | በየዓመቱ | |
| | | የልብስ ሳሙና 250 ግራም | 2 | በየወሩ | |
| | | የውስጥ ልብስ(ለሴት) | 2 | በየዓመቱ | |
| | | ሸሚዝ/የወንድና የሴት | 2 | በየዓመቱ | |
| | | አጭር ቆዳ ጫማ | 1 | በየዓመቱ | |
| | | ካኪ. ቱታ | 2 | በየዓመቱ | |
| | | የላስቲክ ቦት ጫማ | 2 | በየዓመቱ | |
| | | የላስቲክ ጓንት | 2 | በየዓመቱ | |
| | | ቆብ /የፀሐይ መከላከያ/ | 1 | በየዓመቱ | |
| 7 | ተላላኪ. /ወንድ/ | ኮትና ሱሪ | 2 | በየዓመቱ | |
| | | ሸሚዝ | 2 | በየዓመቱ | |
| | | የልብስ ሳሙና 250 ግራም | 1 | በየወሩ | |
| | | አጭር ቆዳ ጫማ ጥንድ | 2 | በየዓመቱ | |
| | | ሣንጥላ | 1 | በየ2 ዓመቱ | |
| 8 | ተላላኪ. /ሴት/ | ኮትና ጉርድ ቀሚስ | 2 | በየዓመቱ | |
| | | አጭር ቆዳ ጫማ ጥንድ | 2 | በየዓመቱ | |
| | | የልብስ ሳሙና 250 ግራም | 1 | በየወሩ | |
| | | የውስጥ ልብስ | 2 | በየዓመቱ | |
| | | ሸሚዝ | 2 | በየዓመቱ | |

FDRE Pharmaceuticals Fund and Supply Agency Office of Board of Directors

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ሣንጥላ | 1 | በየ2 ዓመቱ | |
| 9 | የፅዳት ሰራተኛ/ወንድ/ | ኮትና ሱሪ | 2 | በየዓመቱ | |
| | | ሸሚዝ | 2 | በየዓመቱ | |
| | | የልብስ ሳሙና 250 ግራም | 2 | በየወሩ | |
| | | አጭር ቆዳ ጫማ ጥንድ | 2 | በየዓመቱ | |
| | | ከጨርቅ የተሰራ ኬፕ | 2 | በየዓመቱ | |
| | | ካኪ ካፓርት ወይም ጋውን | 2 | በየዓመቱ | |
| | | ወፍራም የእጅ ጓንት/ፕላስቲክ/ | 2 | በየዓመቱ | |
| | | የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ | 2 | እንዳለቀ ይጠይቃሉ | |
| 10 | የፅዳት ሰራተኛ/ሴት/ | ጉርድ ቀሚስና ኮት | 2 | በየዓመቱ | |
| | | የውስጥ ልብስ | 2 | በየዓመቱ | |
| | | የልብስ ሳሙና 250 ግራም | 2 | በየወሩ | |
| | | የእጅ ጓንት/ፕላስቲክ/ | 2 | በየዓመቱ | |
| | | ፀጉር መሸፈኛ ጨርቅ ወይም ሻሽ | 2 | በየዓመቱ | |
| | | ካኪ ካፖርት ወይም ጋዎን | 2 | በየዓመቱ | |
| | የፅዳት ሰራተኛ/ሴት/ | አጭር የቆዳ ጫማ | 2 | በየዓመቱ | |
| | | የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ | 2 | እንዳለቀ ይጠይቃሉ | |
| 11 | የመጋዘን ጉልበት ሰራተኛና የፎርክሊፍት ኦፕሬተር /ወንድና ሴት/ | ኮትና ሱሪ | 2 | በየዓመቱ | ለሴት ኮትና ጉርድ ቀሚስ /ሱሪ/ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ሸሚዝ | 2 | በየዓመቱ | የሴት ሸሚዝ |
| | | ካኪ ካፖርት | 2 | በየዓመቱ | |
| | | የልብስ ሳሙና 250 ግራም | 2 | በየወሩ | |
| | | ቆብ /ከላስቲክ የተሰራ/ሄልሜት | 1 | በየዓመቱ | በስራ ቦታ የሚቀመጥ |
| | | የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ | 2 | በየዓመቱ | |
| | | አጭር ቆዳ ጫማ /ጥንድ/ | 1 | በየዓመቱ | |
| | | ሴፍት ሹዝ /የአደጋ መከላከያ ጫማ/ | 1 | በየዓመቱ | |
| | | የበረዶ ቤት ልብስ (ቀዝቀዛ ሰንሰለት ላይ ለሚሰሩ ሰራተኞች ብቻ) | 1 | በየ3 ዓመት | በስራ ቦታ የሚቀመጥ |
| | | የእጅ ጓንት/የቆዳ/ | 2 | በየዓመቱ | |
| | | የፀጉር መሸፈኛ ጨርቅ | 2 | በየዓመቱ | ለሴት ሰራተኞች |
| 12 | የመድኃኒትና የህክምና መገልገያ መሳሪያዎች መጋዘን ኃላፊና ዲስፓቸር | ነጭ ጋውን | 2 | በየዓመቱ | በስራ ቦታ የሚቀመጥ |
| | | ቆብ /ከፕላስቲክ የተሰራ/ሄልሜት | 1 | በየዓመቱ | |
| | | የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ | 2 | በየዓመቱ | |
| | | የልብስ ሳሙና 250 ግራም | 1 | በየወሩ | |
| | | ሴፍት ሹዝ | 1 | በየዓመቱ | ለመጋዘን ኃላፊ |
| | | አንጸባራቂ | 1 | በየዓመቱ | |
| 13 | የመድሃኒትና የህክምና መገልገያ መሳሪያዎች | ነጭ ጋዎን | 2 | በየዓመቱ | |
| | | የልብስ ሳሙና 250 ግራም | 1 | በየወሩ | |

EFDRE Pharmaceuticals Fund and Supply Agency
Office of Board of Directors

| | ስርጭት ባለሙያ | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 14 | ሁለገብ የጥገና ሰራተኞች | ኮትና ሱሪ | 2 | በየዓመቱ | ኮትና ጉርድ ቀሚስ ለሴት |
| | | የዝናብ ልብስ | 1 | በየ3 ዓመቱ | |
| | | ሽሚዝ | 2 | በየዓመቱ | |
| | | የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ | 2 | በየዓመቱ | |
| | | አጭር ቆዳ ጫማ /ጥንድ/ | 1 | በየዓመቱ | |
| | | ሴፍቲ ሹዝ /የአደጋ መከላከያ ጫማ/ | 1 | በየዓመቱ | |
| | | የራስ ቆብ/የፕላስቲክ/ | 1 | በየዓመቱ | |
| | | የልብስ ሳሙና 250 ግራም | 2 | በየወሩ | |
| | | ካኪ. ቱታ | 2 | በየዓመቱ | |
| | | ካኪ. ካፖርት | 1 | በየዓመቱ | |
| | | የእጅ ጓንት/ፕላስቲክና ቆዳ/ | 2 | በየዓመቱ | |
| | | ቦት ጫማ ኘላስቲክ | 1 | በየዓመቱ | |
| | | የበረዶ ቤት ልብስ (ቀዝቀዛ ሰንሰለት ላይ ጥገና ለሚሰሩ (ለየግል) | 1 | በየ3 ዓመት | ቀዝቃዛ ሰንሰለት ጥገና ስልጠና የወሰዱና ጥገናውን ለሚያከናውኑ ብቻ |

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የመድኃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ FDRE Pharmaceuticals Fund And Supply Agency የቦርድ አመራር ጽ/ቤት Office of Board of Directors

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | መበየጃ ዓይን መነጽር | 1 | በየዓመቱ | |
| 15 | የንብረት ክፍል ሃላፊና ረዳት | ካኪ ካፖርት | 2 | በየዓመቱ | |
| | | የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ | 2 | በየዓመቱ | |
| | | የልብስ ሳሙና 250 ግራም | 2 | በየወሩ | |
| | | ዣንጥላ | 1 | በየ2 ዓመቱ | |
| 16 | ለትራንዚት ሰራተኛ የመስክ | የዝናብ ልብስ /ገበር ያለው/ | 1 | በየ3 ዓመቱ | |
| | | የልብስ ሳሙና 250 ግራም | 1 | በየወሩ | |
| | | ካኪ ካፖርት | 2 | በየዓመቱ | |
| | | የሰነድ መያዥ የቆዳ ቦርሳ | 1 | በየ2 ዓመቱ | |
| 17 | የዕቃ ግዢ ሰራተኛ | የዝናብ ልብስ /ገበር ያለው/ | 2 | በየ3 ዓመቱ | |
| | | የልብስ ሳሙና 250 ግራም | 1 | በየወሩ | |
| | | ካኪ ካፖርት | 2 | በየዓመቱ | |
| | | የሰነድ መያዥ /የቆዳ ቦርሳ/ | 1 | በየ2 ዓመቱ | |
| 18 | ነገረ ፈጅ | ዣንጥላ | 1 | በየ2 ዓመቱ | |
| | | የሰነድ መያዥ /የቆዳ ቦርሳ/ | 1 | በየ2 ዓመቱ | |
| 19 | የማባዣና ፎቶ ኮፒ ሰራተኛ /ወንድ/ | ኮትና ሱሪ | 2 | በየዓመቱ | |
| | | ሸሚዝ | 2 | በየዓመቱ | |
| | | ካኪ ካፖርት | 2 | በየዓመቱ | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | የልብስ ሳሙና 250 ግራም | 2 | በየወሩ | |
| | | አጭር ቆዳ ጫማ /ጥንድ/ | 2 | በየዓመቱ | |
| | | የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ | 2 | እንዳለቀ | |
| 20 | የማባዣና ፎቶ ኮፒ ሰራተኛ /ሴት/ | ኮትና ጉርድ ቀሚስ | 2 | በየዓመቱ | |
| | | የውስጥ ልብስ | 2 | በየዓመቱ | |
| | | አጭር ቆዳ ጫማ /ጥንድ/ | 2 | በየዓመቱ | |
| | | ካኪ ካፖርት | 2 | በየዓመቱ | |
| | | የልብስ ሳሙና 250 ግራም | 2 | በየወሩ | |
| | | የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ | 2 | በየዓመቱ | |
| 21 | ገንዘብ ያዥ | ነጭ ጋዋን | 2 | በየዓመቱ | |
| | | የልብስ ሳሙና 250 ግራም | 1 | በየወሩ | |
| 22 | ኢንቮይስ ፀሃፊ | ነጭ ጋዋን | 2 | በየዓመቱ | |
| | | የልብስ ሳሙና 250 ግራም | 1 | በየወሩ | |
| 23 | የስቶክና ሰነድ ክትትል ሰራተኛ | ነጭ ጋዋን | 2 | በየዓመቱ | |
| | | የልብስ ሳሙና 250 ግራም | 1 | በየወሩ | |
| 24 | የላቦራቶሪ ሰራተኞች/ወንድና ሴት/ | አጭር ቡትስ ቆዳ ጫማ | 2 | በየዓመቱ | |
| | | ኬሚካል መከላከያ የአይን መነጽር | 2 | በየዓመቱ | |
| | | ወፍራም የእጅ ጓንት /ፕላስቲክ/ | 2 | በየዓመቱ | |
| | | ፕላስቲክ ሽርጥ | 2 | በየዓመቱ | |
| | | የልብስ ሳሙና 250 ግራም | 1 | በየወሩ | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | የእጅ ፎጣ /ትንሿ/ | 2 | በየዓመቱ | |
| | | የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ | 2 | በየዓመቱ | |
| 25 | የስልክ ኦፕሬተር | ነጭ ጋዋን | 2 | በየዓመቱ | |
| | | የልብስ ሳሙና 250 ግራም | 1 | በየወሩ | |
| 26 | የሂሳብ ሰነድ ክትትል ሰራተኛ/ | ነጭ ጋዋን | 2 | በየዓመቱ | |
| | | የልብስ ሳሙና 250 ግራም | 1 | በየወሩ | |
| | | የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ | 2 | በየዓመቱ | |
| 27 | ሪከርድና ማህደር ሰራተኛ | ነጭ ጋዎን | 2 | በየዓመቱ | |
| | | የልብስ ሳሙና 250 ግራም | 1 | በየወሩ | |
| | | የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ | 2 | በየዓመቱ | |
| 28 | የህትመት ባለሙያ | ነጭ ጋዎን | 2 | በየዓመቱ | |
| | | የልብስ ሳሙና 250 ግራም | 1 | በየወሩ | |

## 8. የወተት አበል የሚሠጣቸው የሥራ መደቦች ዝርዝር

| ተ.ቁ | የሥራ መደቡ መጠሪያ | መጠን በቀን (በሊትር) | ምርመራ |
|---|---|---|---|
| 1. | የፎቶኮፒና ማባዣ ሠራተኛ | ½ ሊትር | ኤጀንሲው ወተት በአይነት ያቀርባል ወይም በወቅቱ የገበያ ዋጋ ይከፍላል። |
| 2. | የላብራቶሪ ሠራተኛ | ½ ሊትር | |
| 3. | የህትመት ውጤቶች ዝግጅት ባለሙያ | ½ ሊትር | |

- ኤጀንሲው ለእያንዳንዱ ሰራተኛ በወር አንድ የንፅህና ወረቀት /ሶፍት/ና 80 ግራም የንጽህና ሳሙና በየወሩ ይሰጣል።
- ለመድኃኒትና ንብረት መጋዝን ጉልበት ሰራተኞች፤ ለተሸከርካሪና ሁለገብ ጥገና ባለሙያዎችና አትክልተኛ ሰራተኞች 80 ግራም 1 የገላ ሳሙና በተጨማሪ በየወሩ ይሰጣል።